የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ
ADDIS NEGARI GAZETA
OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሰላሳ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፸፯
አዲስ አበባ ሰኔ ፲ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ/ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32th Year No.77
Addis Ababa 17th day of Jul, 2024

**ማውጫ**

**ደንብ ቁጥር ፻፷፯/፪ሺ፲፮**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር ባለስልጣን አደረጃጀት፣ አሰራር እና የፓራሚሊተሪ ሠራተኞች አስተዳደር ደንብ (ማሻሻያ) ደንብ**

ገፅ..........................................፫ሺ፬፻፲፪

**CONTENTS**

**Regulation No. 167/2024**

**The Addis Ababa City Administration Law Enforcement Authority Organization, Procedures and Paramilitary Personnel Management Regulation (Amendment) Regulation**

Page ……………………..………...……...……… 3412

## ደንብ ቁጥር ፻፷፯/፪ሺ፲፮

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር ባለስልጣን አደረጃጀት፣ አሰራር እና የፓራሚሊተሪ ሠራተኞች አስተዳደር ደንብ (ማሻሻያ) ደንብ

በከተማው ውስጥ የለሙ ፓርኮች፣ ኮሪደሮች፣ መንገዶችና ተጓዳኝ ልማቶች ካላቸው ከፍተኛ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አከባቢያዊ ጠቀሜታ በተጨማሪ ለከተማችን ጽዳት፣ ውበትና መልካም ገጽታ የላቀ አስተዋጽኦ ያላቸው በመሆኑ ጽዳታቸውን፣ ውበታቸውንና መልካም ገጽታቸውን የሚያበላሹ ተግባራትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና አስተዳደራዊ እርምጃ ለመውሰድ በሚያስችል መልኩ ሥራ ላይ የቆየውን የደንብ ማስከበር ሕግ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

## Regulation No. 167/2024

## The Addis Ababa City Administration Law Enforcement Authority Organization, Procedures and Paramilitary Personnel Management Regulation (Amendment) Regulation

**WHEREAS,** it has been found necessary to amend the regulation that has been in operation to the high social, economic and environmental importance of parks, corridors, roads and related developments in the city, they contribute to the cleanliness, beauty and good appearance of our city, so as to prevent, control and take administrative action against activities that damage their cleanliness, beauty and good appearance.

ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፹፬/፪ሺ፲፮ አንቀጽ ፺፬ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ ‹‹የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር ባለስልጣን አደረጃጀት፣ አሰራር እና የፓራሚሊተሪ ሠራተኞች አስተዳደር ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፻፶/፪ሺ፲፭ (ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር ፻፷፯/፪ሺ፲፮» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጉም**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. "ደንብ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር ባለስልጣን አደረጃጀት፣ አሰራር እና የፓራሚሊተሪ ሠራተኞች አስተዳደር ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፻፶/፪ሺ፲፭ ነው፤

፪. በዚህ ደንብ ውስጥ የተጠቀሱ ቃላት ወይም ሐረጎች የከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ ባወጣቸው አግባብ ባላቸው ደንቦች ላይ የተሰጡት ትርጓሜዎች እንደአግባብነቱ ለዚህ ደንብም ያገለግላሉ፡፡

**፫. ማሻሻያ**

፩. የደንቡ አንቀጽ ፲፭፣ ፲፮፣ ፲፯፣ እና ፲፰ ተሰርዘው በአዲስ አንቀጽ ፲፭፣ ፲፮፣ ፲፯ እና ፲፰ ተተክተዋል፤

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 94 of the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment to re-specify the power and duties of the thereof Proclamation No. 84/2023, the Cabinet of Addis Ababa City Government has issued this Regulation.

**1. Short title**

This regulation may be cited as "Regulation No. 150/2023(Amendment) Regulation No. 167/2024 issued to determine the organization, procedure and management of paramilitary personnel of the Addis Ababa City Administration.

**2. Meaning**

In this regulation, unless the context of the word gives another meaning:-

1. "**Regulation"** means the regulation No. 150/2023 issued to determine the organization, procedure and management of paramilitary personnel of the Addis Ababa city administration's law enforcement authority.
2. The interpretations of words or phrases mentioned in this regulation in the relevant regulations issued by the City Administration Cabinet shall apply to this regulation as appropriate.

**3. Amendment**

1. Articles 15, 16, 17 and 18 of the regulation are deleted and replaced by new articles 15, 16, 17 and 18;

፲፭. ስለአስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድ

፩. በወንጀል ሕግ እና በሌሎች ሕጎች የተመለከተው የወንጀል ወይም የደንብ መተላለፍ ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ ይህንን ደንብ በተላለፈ ማንኛውንም ሰው ላይ፡-

ሀ) እንደ ጥፋቱ ሁኔታ ድርጊቱን የማስቆም፣ የማዘጋት፣ የማሸግ፣ የማስነሳት፣ የንግድ ሥራ ፈቃድ ወይም የግንባታ ፈቃድ እንዲሰረዝ የማድረግ፣ የውሃ አቅርቦት እንዲቋረጥ ስልጣን ላላቸው ተቋማት በጽሑፍ የማሳወቅ እና የገንዘብ ቅጣት የመክፈል አቅም የሌላቸው መሆኑ በጽሕፈት ቤቱ የተረጋገጠላቸውን ተቀጪዎች አካባቢውን የማጸዳት ወይም አቅምን ያገናዘበ አካላዊ እንቅስቃሴ የማሰራት እርምጃ ይወስዳል፤

ለ) ከደንቡና ከዚህ ደንብ ጋር አባሪ በተደረገው ሰንጠረዥ ወይም በሌሎች አግባብ ባላቸው ሕጎች መሰረት አስተዳደራዊ ቅጣት ይቀጣል፤

፪. በዚህ ደንብ መሠረት አስተዳደራዊ ቅጣት የተጣለበት ማንኛውም ደንብ የተላለፈ ሰው በደንብ መተላለፍ ክትትል፣ ቁጥጥር እና እርምጃ አወሳሰድ ኦፊሰር የተሰጠውን አስተዳደራዊ ቅጣት ማስታወቂያ ወረቀት በመያዝ ወዲያውኑ ጥፋቱ በተፈፀመበት የወረዳው ጽህፈት ቤት ቀርቦ በሶስት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣቱን ገቢ ማድረግ እና የተጣለበትን ሌላ ቅጣት መፈጸም አለበት፤

15. Taking administrative action

1. Without prejudice to the penal code or code violation penalties stipulated under the penal code and other laws, the authority shall take the following measures on any individual:

a) take measures of stop the action, close, seal, remove and cancel the business license or construction license, notify in writing to the institutions that have authority to cut off the water supply, and clean up the area or carry out physical activity considering the capacity of the violator who have been confirmed by the office as not being able to pay a fine. according to the nature of the offense;

b) fine administrative penalties according to the schedule annexed with this regulation or other relevant laws;

2. Any transgressor who is requested to pay an administrative penalty as per this regulation should bear the notice issued by the code violation follow-up, control, and measure-taking officer and appear in person at the woreda office where the offense was committed and pay the administrative penalty within three consecutive working days;

፫. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ ቢኖርም የደንብ መተላለፍ የፈጸመው ሰው የገንዘብ ቅጣት የመክፈል አቅም የሌለው መሆኑ በባለሥልጣኑ ሲረጋገጥ ደንብ ተላላፊው አካባቢውን ያጸዳል ወይም አቅሙን ያገናዘበ አካላዊ እንቅስቃሴ ይሰራል ወይም ሌላ የጉልበት ሥራ ይሰራል፤

፬. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እንደተጠበቀ ሆኖ የደንብ መተላለፍ በተፈጸመበት ቦታ ቋሚ አድራሻ የሌላቸው ደንብ ተላላፊዎችን በደንብ መተላለፍ ክትትል፣ ቁጥጥር እና እርምጃ አወሳሰድ ኦፊሰር የቅጣት ገንዘቡን ከፖሊስ ጋር በመሆን እንዲከፍሉ ያደርጋል፤

፭. የቅጣት ማስታወቂያ ለመቀበል ፍቃደኛ ካልሆነ እንደተቀበለ ተቆጥሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) ድንጋጌ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

፮. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት አስተዳደራዊ መቀጮውን ገቢ ያላደረገ ሰው የተጣለበትን የቅጣት መቀጮ መጠን እጥፍ እንዲከፍል ይደረጋል፤

፯. እንደጥፋቱ ክብደት እና እንደፈጻሚው ግንዛቤ ደረጃ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለሥልጣኑ ደንብ ተላላፊው የፈጸመውን ጥፋት እና የተወሰነበትን አስተዳደራዊ ቅጣት በመገናኛ ብዙሃን ለህዝብ ይፋ ያደርጋል፤

፰. ባለሥልጣኑ በደንቡ እና በዚህ ደንብ የተደነገጉ ጥፋቶች መፈጸማቸውን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን በተለያየ ዘዴ የማደራጀት እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማስረዳት ኃላፊነት አለበት፤

3. Notwithstanding the provision of sub-Article (2) of this article, when the authority confirms that the person who committed the violation has no capacity to pay the fine, the violator cleans the area or does physical activity or other labor according to his ability;

4. Subject to sub-Article (2) of this article, the monitoring, control and action-taking officer of the violators who do not have a fixed address at the place where the violation occurred shall pay the fine together with the police;

5. If he refuses to accept the notice of penalty, he shall be deemed to have received it and shall be enforced according to the provisions of sub Article (6) of this article;

6. According to sub-Article (2) of this article, a person who does not pay the administrative fine will be made to pay double the amount of the fine imposed;

7. Depending on the seriousness of the offense and the level of awareness of the offender, when necessary, the authority will publicize the offense committed by the violator and the administrative penalty imposed through the media;

8. The authority is responsible for organizing the evidence that proves the commission of the offenses stipulated by the regulation and this regulation in different ways and explaining it when necessary;

፱. ባለሥልጣኑ አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ የተያዘን ወይም እየተያዘ ያለን የመንግስት መሬት ያስለቅቃል፣ ያለግንባታ ፈቃድ የተገነባን ወይም እየተገነባ ያለን ግንበታ ያፈርሳል፣

፲. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) መሠረት መቀጮውን ገቢ ለማድረግ ያልቻለ ወይም ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው በቅጣት ሰንጠረዥ የተቀመጠውን የመቀጮ መጠን እጥፍ እንዲከፍል እና እስከ ሶስት ወር የሚደርስ የማረፊያ ቤት እስራት እንዲቀጣ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ እንዲቀርብበት ይደረጋል፡፡

**፲፮. <u>ስለተደጋጋሚ ጥፋትና አስተዳደራዊ ቅጣት</u>**

ማንኛውም ደንብ ተላላፊ የተወሰነበትን ቅጣት ከፈጸመበት ቀን ጀምሮ በተደጋጋሚ ተመሳሳይ የደንብ መተላለፍ የፈፀመ እንደሆነ፡-

፩. በመጀመሪያ ደንብ መተላለፍ በቅጣት ሰንጠረዥ የተገለጸውን አስተዳደራዊ የገንዘብ መቀጮ እጥፍ ይከፍላል፣

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ) የንግድ ሥራ የሚያከናውን ከሆነ የንግድ ሥራ ፈቃድ ይሰረዛል፣ የውሃ አቅርቦት ይቋረጣል፣

ለ) የግንባታ ሥራ የሚያከናውን ከሆነ የግንባታ ፈቃዱ ይሰረዛል፣ የውሃ አቅርቦት ይቋረጣል፣

ሐ) አሽከርካሪ ከሆነ የመንጃ ፈቃዱ ይሰረዛል፣

9. The authority vacates government land that has been occupied or is being occupied without the permission of the appropriate body;

10. According to sub-Article (6) of this article, a person who is unable or unwilling to pay the fine shall be charged twice the amount of fine set in the penalty table and shall be sentenced to imprisonment of up to six months.

**16. <u>Recurrent Offences and Administrative Penalties</u>**

If any transgressor commits similar code violations starting from the day he has paid the imposed fine in full or partially, he shall be forced to pay;

1. the administrative fine indicated under the penalty schedule for the first code violation;
2. Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article:
   a) The business license will be cancelled if the individual is conducting business; Water supply will be cut off.
   b) If he carries out construction work, the construction permit will be cancelled; Water supply will be cut off.
   c) If he is a driver, his driving license will be cancelled;

መ) መኖሪያ ቤት ከሆነ የውሃ አቅርቦት ይቋረጣል፣

ሠ) መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ከሆነ የውሃ አቅርቦት ይቋረጣል፣

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት ክፍያውን ካልፈጸመ ወይም ግዴታውን ካልተወጣ ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ በመመስረት ክፍያውን እንዲከፍል ወይም ግዴታውን እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

**፲፯. <u>ቅጣትን ስለማስፈፀም</u>**

፩. ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የተወሰነውን አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት እና የተጣለበትን ሌላ አስተዳደራዊ ቅጣት በተመለከተ፡-

ሀ) አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣቱን በወረዳው ጽሕፈት ቤት ያስፈጽማል፣

ለ) አካባቢውን እንዲያጸዳ ወይም አካላዊ እንቅስቃሴ እንዲያደርግ ወይም ሌላ የጉልበት ሥራ እንዲሰራ የተወሰነበትን ደንብ ተላላፊ የደንብ ጥሰቱ የተፈጸመበት ቦታ ላይ ያስፈጽማል፣ የአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን ከባለሥልጣኑ የድጋፍ ጥያቄ ሲቀርብለት ይተባበራል፣

d) The water supply will be cut off if it concerns a residential house;

e) If it is a governmental or non-governmental organization, water supply will be cut off;

3. if the person fails to pay the fine or the obligation is not fulfilled according to Sub-Article (1) and (2) of this Article, he will be charged to appear before the relevant court and forced to pay the thereof in collaboration with the relevant organ.

**17. <u>Executing the penality</u>**

1. The authority shall, in accordance with Sub-Article (2) of Article 15 of this regulation, with regard to the administrative fines and other administrative fines imposed:

a) execute the administrative fine at the Wereda office

b) execute a regulation violator to clean up the area or perform physical activity or other labor at the location where the violation occurred; The Addis Ababa City Police Commission cooperates with requests for support from the authorities;

፪. ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገጉ አስተዳደራዊ ቅጣቶችን ለደንብ ተላላፊው ፈቃድ ለሰጡ ወይም አገልግሎት ለሚያቀርቡ አስፈጻሚ ተቋማት ውሳኔውን በመላክ እንዲፈጸም ያደርጋል፤

፫. ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፭ ንዑስ አንቀጽ (፯) መሠረት የተወሰነው አስተዳደራዊ ቅጣት ተፈጻሚ እንዲሆን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮሚዩኒኬሽን ቢሮ ይልካል፤ መፈጸሙን ያረጋግጣል፤

፬. ከባለሥልጣኑ አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲያስፈጽሙ ውሳኔ የተላከላቸው አስፈጻሚ ተቋማት ቅጣቱን ያስፈጽማሉ፤

፭. የወረዳው ጽህፈት ቤት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተመለከተው መሠረት ተገቢው ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት አስተዳደራዊ መቀጮውን ገቢ ያላደረገውን ወይም ያልፈጸመውን ማንኛውም ደንብ ተላላፊ በደንቡ ላይ የተገለጸው አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲፈጽም ለሚመለከተው አካል ክስ እንዲመሰረትበት ማስረጃውን አደራጅቶ ይልካል፤

፮. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት ክስ እንዲመሠረት የተደረገበት ደንብ ተላላፊ እንደአግባቡ በማህበራዊ ፍርድ ቤት ወይም ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክስ በመመስረት እንዲፈጸም ይደረጋል፡፡

2. The authority shall send the decision to enforce the administrative penalties stipulated in Sub-Article (2) of Article 16 of this regulation to the executive institutions that have given permission or provide services to the violator;
3. The authority shall send to Addis Ababa City Administration Communication Office so that the determined administrative penalty may be enforced according to Article 15 Sub-Article (7) of this Regulation;
4. Executive institutions to whom a decision has been sent to enforce an administrative penalty from the authority shall enforce the penalty;
5. The Woreda office shall organize and send the evidence to the relevant party to be charged with the administrative penalty specified in the regulation for any regulation violator who has not paid the administrative fine or has not paid the administrative fine according to the Sub-Article (2) of Article 15 of this regulation
6. According to Sub-Articele (5) of this article, the violation of the regulation will be prosecuted by the social court or the competent court.

## ፲፰. ስለአቤቱታ አቀራረብ

፩. ይህንን ደንብ በመተላለፉ በተሰጠው ቅጣት ፈቃዱ የተሰረዘበት ወይም የውሃ አቅርቦት የተቋረጠበት ማንኛውም ሰው ቅሬታውን ለወረዳው ጽህፈት ቤት ለማቅረብ ይችላል፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ቅሬታ የተቀበለ የወረዳ ጽህፈት ቤት በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን መርምሮ ይወስናል፤ ውሳኔውን ከነምክንያቱ በጽሁፍ ለአቤቱታ አቅራቢው ያሳውቃል፤

፫. ቅሬታ አቅራቢው ያቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት ካገኘና አስተዳደራዊ ውሳኔው ሊሻር ይገባል የሚል በቂ ምክንያት ካለው የወረዳው ጽህፈት ቤት የተሰጠውን አስተዳደራዊ ውሳኔ በመሻር ፈቃዱን ለሰረዘው ወይም አገልግሎቱን ላቋረጠው አስፈጻሚ ተቋም ፈቃዱ እንዲመለስ ወይም የተቋረጠው የውሃ አቅርቦት እንዲቀጠል ይደረጋል፤

፬. ይህንን ደንብ በመተላለፍ አስተዳደራዊ ቅጣት የተጣለበት ማንኛውም ሰው መከፈል ከሚገባው የመጨረሻው ቀን ቀጥሎ ባሉት ሁለት የስራ ቀናት ጥፋቱ በተፈፀመበት ወረዳ ጽህፈት ቤት አቤቱታውን ሊያቀርብ ይችላል፤

## 18. Complaints Submittal

1. Any person whose license has been canceled or whose water supply has been cut off as a result of violating this regulation could lodge his complaint with the Wereda office;
2. According to Sub-Articele (1) of this article, the woreda office that receives a complaint will examine and decide the complaint within five working days; He shall inform the complainant of his decision and the reasons thereof in writing;
3. If the complaint submitted by the complainant is accepted and there is sufficient reason that the administrative decision should be revoked, the Woreda office will revoke the administrative decision given to the executive institution that canceled the license or terminated the service, and the license will be returned or the interrupted water supply will be resumed;
4. Any person who has been imposed an administrative fine for violating this regulation can submit the petition at the office of the district where the offense was committed within two working days following the last day of payment;

፭. የወረዳ ጽህፈት ቤት የቀረበውን አቤቱታ ከዚህ ደንብና ሌሎች አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር አገናዝቦ በመመርመር በቀረበው አቤቱታ ላይ በ፭ (በአምስት) የስራ ቀናት ውስጥ ይወስናል፣ ውሳኔውን ከነምክንያቱ በጽሁፍ ለአቤቱታ አቅራቢው ያሳውቃል፡፡

፪. የደንቡ የቅጣት ሰንጠረዥ ፪ ተሰርዞ በሚከተለው የቅጣት ሰንጠረዥ ፪ ተተክቷል፣

፫. የደንቡ የቅጣት ሰንጠረዥ ፬ ተራ ቁጥር ፩ ተሰርዞ በዚህ ደንብ የቅጣት ሰንጠረዥ ፪ ተራ ቁጥር ፴፭ ተተክቷል፣

፬. የደንቡ የቅጣት ሰንጠረዥ ፫ ተራ ቁጥር ፲፩ ተሰርዞ በዚህ ደንብ የቅጣት ሰንጠረዥ ፪ ተራ ቁጥር ፴፮ ተተክቷል፣

**፬.ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከሰኔ ፲ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፲ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

5. The woreda office will examine the petition against this regulation and other relevant laws and make a decision on the petition within 5 (five) working days and notifies the complainant of the decision and the reasons in writing.

2. Penalty schedule 2 of the regulation is deleted and replaced by the following new penalty schedule 2;
3. row number 1 of the penalty schedule 4 of the regulation is deleted and replaced by row number 35 of penalty schedule 2 of this regulation;
4. row number 11 of the penalty schedule 3 of the regulation is deleted and replaced by row number 36 of penalty schedule 2 of this regulation;

**4. Effective Date**

This regulation shall enter into force as of this 17th day of June 2024.

**Addis Ababa, this 17th day of June 2024**

**Adanech Abebe,**

**Mayor of Addis Ababa city**

## "የቅጣት ሰንጠረዥ 2

## በሕገወጥ መንገድ ፍሳሽም ሆነ ደረቅ ቆሻሻ ማስወገድ

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነቶች | የቅጣት ክፍያ መጠን | ከህገ-ወጥ ድርጊት ፈጻሚዉ የሚጠበቅ |
|---|---|---|---|
| 1 | ማንኛውም ሰው ያመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ በግቢው ውስጥ በአግባቡ አለመያዝ፤ በዓይነት አለመለየት፤ ማዝረክረክ፤ ለጤናና የአካባቢ ገጽታ በሚጎዳ መልኩ ማከማቸት፤<br>1.1. ከመኖሪያ ቤት ከሆነ<br>1.2. ከድርጅት ከሆነ | ብር 2000.00<br>ብር 50,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያከማቸውን ደረቅ ቆሻሻ ማንሳት |
| 2 | ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት ሰጭ ድርጅት/ማህበር<br>2.1 ደረቅ ቆሻሻ ሲሰበስብ በአካባቢው ላይ ካንጠባጠበ ወይም የአካባቢውን ገጽታ ካበላሸ<br>2.2 በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ለደንበኛው ተገቢውን አገልግሎት ካልሰጠ<br>2.3 ከጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ እውቅና ውጭ የአገልግሎት ክፍያ ከደንበኛው ከተቀበለ<br>2.4 ጊዜያዊ የደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫ ቦታዎችን እስከ 5 ሜትር ዙሪያ ድረስ ጽዱ ካላደረገ | ብር 25000.00<br>ብር 50,000.00<br>ብር 50,000.00<br>ብር 50,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያቆሸሸውን አካባቢ ማጽዳት |
| 3 | ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውል ደረቅ ቆሻሻ ከጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ህጋዊ እውቅና ሳይኖረው በግል፤ በማህበርም ይሁን በድርጅት ስም በግቢ ውስጥ ወይም በክፍት ቦታ ላይ ያከማቸ ማንኛውም ሰው፤ | ብር 20,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያከማቸውን ቆሻሻ ማስወገድ |

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነቶች | የቅጣት ክፍያ መጠን | ከህግ-ወጥ ድርጊት ፈጻሚዉ የሚጠበቅ |
|---|---|---|---|
| 4 | በመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ዘርፍ የተሰማራ ግለሰብ፣ ማህበር ወይም ድርጅት ለመልሶ መጠቀምና ኡደት የዋለ ደረቅ ቆሻሻ መረጃ ለሚጠይቀው ህጋዊ አካል ካልሰጠ፤ | ብር 2,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና መረጃ መስጠት |
| 5 | በደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ውስጥ ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውል ደረቅ ቆሻሻ የለቀመ ወይም ያከማቸ ማንኛውም ሰው፤ | ብር 2,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያከማቸውን ቆሻሻ ማንሳት |
| 6 | ደረቅ ቆሻሻን ከግቢው አውጥቶ ባልተፈቀደ ቦታ የጣለ ወይም ያስቀመጠ ማንኛውም ሰው፤<br>6.1 የመኖሪያ ቤት ቆሻሻ ከሆነ<br>6.2 የኢንዱስትሪ ቆሻሻ ከሆነ<br>6.3 የጤና ተቋም ቆሻሻ ከሆነ<br>6.4 ከሌሎች ድርጅቶች የመነጨ ቆሻሻ ከሆነ | <br><br>ብር 2000.00<br>ብር 50,000.00<br>ብር 30,000.00<br>ብር 10,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና የጣለውን ቆሻሻ ማንሳት |
| 7 | 7.1. ከመኪና ውስጥ የመነጨን ደረቅ ቆሻሻ በማንኛውም ባልተፈቀደ ቦታ ጠርጎ የጣለ ማንኛውም ሰው፤<br>7.2. አሽከርካሪ ወይም ተሳፋሪ ከመኪና ውስጥ ሆኖ በመስኮትም ይሁን በበር በኩል ማንኛውንም ዓይነት ደረቅ ቆሻሻ ወደ ውጭ የወረወረ ወይም የጣለ ማንኛውም ሰው፤ | ብር 5,000.00<br>ብር 2000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና የጣለውን ቆሻሻ ማንሳት |
| 8 | ማንኛውም በመንገድ የሚንቀሳቀስ ሰው የሲጋራ ቁርጥራጭ፣ የሶፍት ወረቀት፣ ፌስታል፣ የጫት ገለባ፣ የፍራፍሬ ተረፈ- | ብር 2000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን |

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነቶች | የቅጣት ክፍያ መጠን | ከህገ-ወጥ ድርጊት ፈጻሚዉ የሚጠበቅ |
|---|---|---|---|
| | ምርቶች፣ የትራንስፖርት ቲኬት፣ የሞባይል ካርዶችን፣ የማስቲካና ከረሜላ ሽፋኖች፣ የመሳሰሉት ጥቃቅን ደረቅ ቆሻሻን ባልተፈቀደ ቦታ ወይም በፓርኮች፣ በአረንጓዴ ቦታ፣ በኮሪደር መሰረተ ልማቶች፣ በመናፈሻ ቦታ፣ በክፍት የሕዝብ መናፈሻ፣ በመንገድ መናፈሻ፣ በመንገድ፣ በመንገድ አካፋይ፣ በመንገድ ዳርቻ፣ በአደባባይ፣ በፕላዛ ቦታ የመንገድ ቱቦ፤ ድልድይ ውስጥ፤ በክፍት ቦታ በመሳሰሉት ላይ ከጣለ ወይም ከወረወረ፤ | | መክፈልና ያቆሸሸውን አካባቢ ማጽዳት |
| 9 | 9.1 ማንኛውም ሰው ከሚመለከተው አካል ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው አሸዋ፣ አፈር፣ ሳር፤ ቅጠላ ቅጠል፤ የግንባታ ፍርስራሽ ባልተፈቀደ ቦታ ላይ በማስቀመጥ አካባቢን ካቆሸሸ፤<br><br>9.2 በመንገድ ወይም በሌላ ባልተፈቀደ ቦታ በፓርኮች፣ በአረንጓዴ ቦታ፣ በኮሪደር መሰረተ ልማቶች፣ በመናፈሻ ቦታ፣ በክፍት የሕዝብ መናፈሻ፣ በመንገድ መናፈሻ፣ በመንገድ፣ በመንገድ አካፋይ፣ በመንገድ ዳርቻ፣ በአደባባይ፣ በፕላዛ ቦታ እና በመሳሰሉት ቁጠማ፤ ሳር፤ የበቆሎ ሽፋን ወይም ቆረቆንዳ፤ ጭድ፤ ሸንኮራ አገዳ፤ የሸንብራና የባቄላ እሸት ገለባ፤ የፍራፍሬ ልጣጭ እና የመሳሰሉት ሲሸጥ አካባቢውን ያቆሸሸ ወይም ግብዓቱን ተጠቅሞ ተረፈ ምርቱን የጣለ ማንኛውም ሰው፤ | ብር 25,000.00<br><br>ብር 5000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያቆሸሸውን አካባቢ ማጽዳት |
| 10 | አፈር፤ አሸዋ፤ ጠጠር፤ ሳርና ሌሎች ተረፈ ምርቶች በተሽከርካሪ ሲጓጓዝ በሸራ ወይም በመረብ ሳይሸፍን ወይም በአግባቡ ባለመሸፈኑ ምክንያት አካባቢውን ያቆሸሸ ማንኛውም ሰው፤ | ብር 10,000.00 ለግለሰብ<br>ብር 25,000.00 ለድርጅት | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ያቆሸሸውን አካባቢ ማጽዳት |

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነቶች | የቅጣት ክፍያ መጠን | ከህጉ-ወጥ ድርጊት ፈጻሚዉ የሚጠበቅ |
|---|---|---|---|
| 11 | የጽዳት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት/ማህበር ኤጀንሲው ለደረቅ ቆሻሻ ጊዜያ ማቆያ ወይም ማስወገጃነት ከፈቀደው ቦታ ውጭ ማንኛውንም ደረቅ ቆሻሻ ካስቀመጠ፤ ከጣለ፤ ካቃጠለ ወይም ከቀበረ | ብር 20,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያቆሸሸውን አካባቢ ማጽዳት |
| 12 | ከመፀዳጃ ቤት ውጭ በማንኛውም ቦታ ሽንት መሽናት ወይም መጸዳዳት፤ | ብር 2,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያቆሸሸውን አካባቢ ማጽዳት |
| 13 | በመንገድ ዳር በሚቀመጡ የጥቃቅን ደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫ እቃዎችን<br>1.1. ያለ ህጋዊ ፈቃድ ከአካባቢው ያስወገደ፤ ነቅሎ የጣለ፤ ያበላሸ፤ የሰበረ፤ የወሰደ፤ ለሌላ አገልግሎት ያዋለ ማንኛውም ሰው፤<br>1.2. ማስታወቂያ የለጠፈ ወይም በላያቸው ላይ እቃ ያስቀመጠ ማንኛውም ሰው፤ | ብር 50,000.00<br><br>ብር 5000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ንብረቱን መመለስ ወይም ማስታወቂያውን ማንሳት |
| 14 | በአገልግሎት ሰጭ ተቋማትና የማምረቻ ድርጅቶች ተገቢ የሆነ የጥቃቅን ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃ በግቢው ውስጥና በአካባቢው አለማስቀመጥ፤ | ብር 50,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ደስት ቢን ማስቀመጥ |
| 15 | ከቤት እንስሳት የሚወጡ እዳሪ (ኩስ፤ ፍግ፤ እበት)፤ እና የእንስሳት የምግብ ተረፈ ምርቶችን ባልተፈቀደ ቦታ የጣለ ወይም አካባቢውን ያቆሸሸ ማንኛውም ሰው፤ | ብር 50,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና የጣለውን ቆሻሻ ማንሳትና አካባቢውን ማጽዳት |

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነቶች | የቅጣት ክፍያ መጠን | ከህገ-ወጥ ድርጊት ፈጻሚዉ የሚጠበቅ |
|---|---|---|---|
| 16 | የተለያዩ እንስሳትን ባልተፈቀደ ቦታ ላይ በማጸዳዳት አካባቢውን ማቆሸሽ፤ | ብር 5000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ቆሻሻ ማንሳት |
| 17 | ሳር፤ ቅጠላ ቅጠል፤ አፈር፤ አሸዋና ሌሎች ተረፈ ምርቶችን ሳይሸፍን በጋማ ከብት በማጓጓዝ አካባቢውን ያቆሸሸ ወይም ያዝረከረከ ማንኛውም ሰው፤ | ብር 2000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና የጣለውን ቆሻሻ ማንሳት |
| 18 | የሞተ እንስሳን ባልተፈቀደ ቦታ የጣለ ማንኛውም ሰው፤ | ብር 25000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና የጣለውን ቆሻሻ ማንሳት |
| 19 | በአትክልትና ፍራፍሬ የገበያ ማዕከላትና የተለያዩ የገበያ ማዕከላት የሚገኙ ግለሰቦችና ድርጅቶች የተረፈ ምርታቸውን ደረቅ ቆሻሻ<br>19.1 ከንግድ ማዕከሉ ግቢ ውጭ ወይም መንገድ ዳር ተረፈ ምርት ቆሻሻ ያከማቸ ያስቀመጠና የጣለ፤<br>19.2 ከተሽከርካሪ ላይ አትክልትና ፍራፍሬ ሲጭንና ሲያወርድ የሚወዳድቁ የአትክልት ትርፍራፊ ቆሻሻ ወዲያው ያላጸዳ፤<br>19.3 የገበያ ማዕከሉን ደረቅ ቆሻሻ በራሱ ወጭ ሰብስቦ ኤጀንሲው በፈቀደው ህጋዊ ማስወገጃ ቦታ ወይም የመልሶ መጠቀምና | <br>ብር 50,000.00<br>ብር 5,000.00<br>ብር 50,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና አካባቢውን ማጽዳት |

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነቶች | የቅጣት ክፍያ መጠን | ከህገ-ወጥ ድርጊት ፈጻሚዉ የሚጠበቅ |
|---|---|---|---|
| | ኡደት ማእከላት ያላስወገደ፤<br>19.4 ከመደብሩ ፊት ለፊት የመደብር ጥራጊ፤ በሽያጭ ወቅት የተከሰቱ የእቃ ማሸጊያ፤ የጫት ገራባ፤ ካርቶን የመሳሰሉትን ካስቀመጠ፤ | ብር 20,000.00 | |
| 20 | 20.1 ከግንባታ ወይም ከፍርስራሽ የሚመነጭ ደረቅ ቆሻሻን ባልተፈቀደ ቦታ የጣለ ግለሰብ/ድርጅት<br>20.2 በከግንባታ ማዕከል በተሽከርካሪ ጎማ እንቅስቃሴ ወይም በጭነት ወቅት በሚንጠባጠብ አፈር፤ ጭቃ፤ ፍርስራሽ የመሳሰሉትን ምክንያት በሚፈጠር ቆሻሻ አካባቢውና መንገዱ ያበላሸ የግንባታ ባለቤት | ብር 5,000.00 ለአሻከርከሪ/ ብር 50000.00 ለድርጅት<br>ብር 5,000.00 ለአሽከርካሪ/ ብር 50000.00 ለድርጅት | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያቆሸሸውን አካባቢ ማጽዳት |
| 21 | የአጥንትና የስጋ ተረፈ ምርትን ባልተፈቀደ ቦታ የጣለ<br>ግለሰብ/<br>ድርጅት | ብር 5,000.00<br>ብር 50,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና የጣለውን ቆሻሻ ማንሳት |
| 22 | ከጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ህጋዊ ፈቃድ ውጭ ማንኛውንም አደገኛ ደረቅ ቆሻሻ ወይም ተገቢነት የሌለውን ደረቅ ቆሻሻ ወደ ማስወገጃ ቦታ፤ ማቃጠያ ማዕከል፤ ቅብብሎሽ ጣቢያ ወይም የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማዕከል ያጓጓዘ ድርጅት/ማህበር/ግለሰብ/ተቋም፤ | ብር 50,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያመጣውን ቆሻሻ መመለስ |

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነቶች | የቅጣት ክፍያ መጠን | ከህገ-ወጥ ድርጊት ፈጻሚዉ የሚጠበቅ |
|---|---|---|---|
| 23 | አገልግሎት የማይሰጡ የኤሌክትሮኒክስ ቁሳቁሶችን በተለየ መልኩ በመለየት በአግባቡ እና አካባቢውን በማይበክል መንገድ እንዲወገድ ያላደረገ ማንኛውም ሰው፤ | ብር 10,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና የጣለውን ቆሻሻ ማንሳት |
| 24 | ከመኖሪያ ቤት ወይም ከድርጅት ግቢ ውጭ ያለውን የአካባቢ ንጽህና አረንጓዴ አድርጎ አለመጠበቅ፡-<br>24.1. ከመኖሪያ ቤት አጥር ግቢ ውጭ እስከ 5 ሜትር ርቀት አለማጽዳት፤<br>24. 2. ከድርጅት/ተቋም አጥር ግቢ ውጭ እስከ 10 ሜትር አለማጽዳት፤ | ብር 20000.00<br>ብር 100,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና አካባቢውን ማጽዳት |
| 25 | ወቅታዊና ልዩ ዝግጅት አከናውኖ በዓሉ ሲጠናቀቅ በዕለቱና ወዲያው ዝግጅቱ የተከናወነበትን አካባቢ ከቆሻሻ ያላጸዳ የፕሮግራሙ አዘጋጅ፤ | ብር 50,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያቆሸሸውን አካባቢ ማጽዳት |
| 26 | ዓመታዊ፤ ወርሃዊና ሳምንታዊ የእምነት በዓላት ሲከናወኑ ዝግጅቱ ሲጠናቀቅ የዝግጅቱ ባለቤት በዕለቱና ወዲያው አካባቢውን ካላጸዳ፤ | ብር 20,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያቆሸሸውን አካባቢ ማጽዳት |
| 27 | የታክሲና ሚኒባስ ተራ አስከባሪ፤ የፓርኪንግ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት፤ በጫማ ጥገናና ጽዳት (ሊስትሮ) የተሰማራ፤ በእረፍት ቀን (ቅዳሜና እሁድ) መንገድ ላይ የሚነግዱ ነጋዴ፤ ሕጋዊ ፈቃድ ያለው የእንስሳት የግብይት ማዕከላት እና የመሳሰሉትን የሚሰራበትን አካባቢ እስከ 5 ሜትር ዙሪያ | ለግለሰብ ብር 2000.00<br>ለድርጅት ብር 20,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና አካባቢውን ጽዳት |

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነቶች | የቅጣት ክፍያ መጠን | ከህገ-ወጥ ድርጊት ፈጻሚዉ የሚጠበቅ |
|---|---|---|---|
| | ከቆሻሻ ጽዱ ያላደረገ ማንኛውም ሰው፤ | | |
| 28 | የባቡር ሀዲድ የተዘረጋባቸውን መስመሮችና የባቡር ፌርማታዎች ከደረቅ ቆሻሻ እንዲጸዳ ያላደረገ የቀላል ባቡር ድርጅት፤ | ብር 50,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና አካባቢውን ከቆሻሻ ማጽዳት |
| 29 | 29.1 የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ በሚያወጣው የጽዳት ንቅናቄ መመሪያ መሰረት የመንግስት መስሪያ ቤቶች፤ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፤ የእምነት ተቋማት፤ ትምህርት ቤቶች፤ ንግድ ድርጅቶች፤ አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ሰራተኞቻቸውን አስተባብረው በጽዳት ንቅናቄው ተሳታፊ ያላደረገ ተቋም/ድርጅት፤<br>29.2 የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ በሚያወጣው የጽዳት ንቅናቄ መመሪያ መሰረት በመኖሪያ አካባቢው በጽዳት ንቅናቄ ተሳታፊ ያልሆነ አባወራ ወይም እማወራ፤ | ብር 5,000.00<br>ብር 2000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና በንቅናቄ ተሳታፊ መሆን |
| 30 | ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት/ማህበር/ተቋም ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ በሚያወጣው ስታንዳርድ መሰረት ሰራተኞቹ/አባላቱ የደህንነት መጠበቂያ ግብዓት ሳይጠቀም አገልግሎት ከሰጠ ወይም ንጽህናውን ያልጠበቀ የደህንነት መጠበቂያ ግብዓት ተጠቅሞ አገልግሎት ከሰጠ፤ | ብር 5,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ንጹህ የደህንነት መጠበቂያ ግብዓት መጠቀም |
| 31 | 31.1. ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት የሚሰጥ የጽዳት ድርጅት በጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ያልተፈቀደ ደረቅ ቆሻሻ በማስወገጃ ቦታ፤ መልሶ መጠቀም | ብር 50,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ቆሻሻውን |

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነቶች | የቅጣት ክፍያ መጠን | ከህገ-ወጥ ድርጊት ፈጻሚዉ የሚጠበቅ |
|---|---|---|---|
| | ማዕከል ወይም ወደ ማቃጠያ ማዕከላት አንጉዞ ካመጣ፤<br>31.2. ከጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ፈቃድ ውጭ ደረቅ ቆሻሻን ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውጪ ወደ ከተማው ያስገባ ማንኛውም ሰው፤<br>31.3. በመረብ ወይም በሸራ ያልተሸፈነ ደረቅ ቆሻሻ በተሽከርካሪ ጭኖ ወደ በማስወገጃ ቦታ፤ መልሶ መጠቀም ማዕከል ወይም ማቃጠያ ማዕከላት አንጉዞ ያመጣ ድርጅት /ማህበር/ ግለሰብ/ ተቋም፤ | ብር 100,000.00<br>ብር 10,000.00 | ወደ መጣበት ቦታ መመለስ |
| 32 | ማንኛውም የግል ጽዳት ድርጅት ወይም ማህበር ከተመደበበት የስራ ቦታ ወይም ምደባ ውጭ ደረቅ ቆሻሻ ከሰበሰበ፤ | ብር 50,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈል |
| 33 | ሰራተኞች በቸልተኝት ወይም ሆን ብለው በመንገድ ዳር የተተከሉ አትክልት ውሃ ሲያጠጡ አፈር ወደ መንገዱ እንዲወጣ እና መንገድ እንዲቆሽሽ ያደረጉ፤ | ብር 5000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈል |
| 34 | አንድ ተቋም/ድርጅት ከውሀ መውረጃ ቱቦ የተጠረገ ቆሻሻ ከመንገድ ዳር እስከ 2 ቀን ካላነሳ | ብር 20000 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና አካባቢውን ማጽዳት |
| 35 | ማንኛውም ሰው ለግንባታ መከለያ በታጠረ አጥር ወይም በሕንጻ አጥር ላይ ስዕል የሳለ ወይም ጽሁፍ የጻፈ፣ ማስታወቂያ ወይም ጽሁፍ የለጠፈ፣ ያንጠለጠለ፣ በኤሌክትሪክ ወይም በስልክ ምሶሶ፣ በድልድይ ስር ምሶሶ፤ በአፈር | ለግለሰብ ብር 2000 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈል |

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነቶች | የቅጣት ክፍያ መጠን | ከህግ-ወጥ ድርጊት ፈጻሚዉ የሚጠበቅ |
|---|---|---|---|
| | መደገፊያ ግንብ፣ ለግንባታ መከለያ በታጠረ አጥር፣ በሕንጻ አጥር ላይ ማስታወቂያ ወይም ጽሁፍ የለጠፈ | ለድርጅት ብር 25000 | |
| 36 | መኪና ባልተፈቀደ ቦታ በማጠብ ወይም በማሳጠብ አካባቢው እንዲቆሽሽ ያደረገ ማንኛውም ሰው፤ | ያጠበ ብር 2000.00<br>ያሳጠበ ብር 20,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣትና አካባቢውን ማጽዳት |

## Penalty Schedule 2

## Illegal Disposal of Sewerage or Solid Wastes

| No. | Types of offenses | Amount of penalty payment | Amount Expected from the perpetrator of the illegal act |
|---|---|---|---|
| 1 | Anybody who does not properly handle a solid waste that he generated within his premises, identify accordingly, littering, and store it in a way that harms the health and the environment:<br>1.1. From houses<br>1.3. From organizations | <br>Birr 2,000.00<br>Birr 50,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and remove the accumulated solid waste |
| 2 | Any sanitary service providing organization/association:<br>1.1. Littering while collecting solid wastes or make the surrounding messy;<br>1.2. Not properly provide service to customers based on the set standard;<br>1.3. Accept undue service charges from customers without the knowledge of the sanitary management agency;<br>1.4. Failure to clean temporary solid waste storage areas within 5 meters radius; | <br>Birr 25,000.00<br>Birr 50,000.00<br>Birr 50,000.00<br>Birr 50,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the area |
| 3 | Storing solid wastes in a compound or open space for reuse or recycling purpose on individual basis, through association, or in the name of an organization without having a legal permit from the sanitary management agency; | Birr 20,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and remove the accumulated solid waste |
| 4 | Failure to provide information for the request of an authorized body regarding the solid waste used for reuse or recycle purpose by an individual, association or organization; | Birr 2,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and provide the information |

| No. | Types of offenses | Amount of penalty payment | Amount Expected from the perpetrator of the illegal act |
|---|---|---|---|
| 5 | Any person taking or storing solid wastes to be used for reuse or recycle purpose without having a legal license from the solid waste disposal site;; | Birr 2,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and remove the accumulated solid waste |
| 6 | Any person Removal of solid wastes out a compound and disposing or placing it in an authorized place;<br>6.1. If it is a household waste<br>6.2. If it is an industrial waste<br>6.3. If it is a health institution waste<br>6.4. If it is the waste of other organizations | Birr 2,000.00<br>Birr 50,000.00<br>Birr 30,000.00<br>Birr 10,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and remove the accumulated solid waste |
| 7 | 7.1. Any person who disposes of solid waste generated from a vehicle in any unauthorized place;<br>7.2. Disposal of a waste at any place that was generated from cars; | Birr 5,000.00<br>Birr 2000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and remove the accumulated solid waste |
| 8 | Any person moving on the road, cigarette butts, soft paper, Festal, chaat straw, fruit by-products, Transport ticket, mobile cards, gummy candy wrappers, such as small solid waste in unauthorized places or parks; In green space, corridor infrastructure, park space, open public park, road park, road, road divider, road side, public square, plaza place road pipeIn the bridge፣ If he casts or throws upon the like in an open place; | Birr 2000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the place |

| No. | Types of offenses | Amount of penalty payment | Amount Expected from the perpetrator of the illegal act |
|---|---|---|---|
| 9 | 9.1. Placing sands, soils, grass, leaves, construction dumps in an unauthorized place without having a legal permit from the concerned organ and making the place messy;<br>9.2. Any person on roads or other unauthorized places in parks, green spaces, corridor infrastructures, parks, open public parks, road parks, roads, road dividers, roadsides, plazas, plazas and in the like Ketema፤ grass ፤ A corn husk or husk; straw፤ sugar cane; Chickpea and bean straw; Any person who pollutes the environment or disposes of the by-products of using the ingredients while selling fruit peels and the like; | Birr 25,000.00<br><br>Birr 5,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the place |
| 10 | Failure to cover soil, sand, gravel, grass, and other by-products with canvas or net while transporting it and make the place messy; | Birr 10,000.00 for an individual<br>Birr 25,000.00 For an organization | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the place |
| 11 | When a sanitary service providing organization/association places, dumps, burns, or buries any solid waste except the places where the agency allows for the temporary placement or disposal of solid wastes; | Birr 20,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the place |
| 12 | urinating or defecating anywhere other than a toilet; | Birr 2,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the place |
| 13 | Concerning the litterbins that placed on road sides:<br>13.1. Removes, dislocates and throws away, damages, breaks, takes, or uses it for another purpose;<br>13.2. Post advertisements or puts things on it; | Birr 50,000.00<br><br>Birr 5000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and return the property or remove the advertisement |

| No. | Types of offenses | Amount of penalty payment | Amount Expected from the perpetrator of the illegal act |
|---|---|---|---|
| 14 | The failure of service providing institutions and manufacturing organizations to place appropriate litterbins within their compound and the surrounding area; | Birr 50,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and prepare litterbins |
| 15 | Removing wastes of domestic animals and the by-products of their fodders on an unauthorized place or make the place messy; | Birr 50,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and remove the disposed waste and clean the place |
| 16 | Allowing various animals defecate on an unauthorized place and make the place messy; | Birr 5,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and remove the waste |
| 17 | Failure to cover grass, leaves, soils, sand, and other by-products while transporting it by equine and making the place messy or littering; | Birr 2,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and remove the waste |
| 18 | Any person who disposes of a dead animal in an unauthorized place; | Birr 25,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and remove the waste |

| No. | Types of offenses | Amount of penalty payment | Amount Expected from the perpetrator of the illegal act |
|---|---|---|---|
| 19 | Regarding the solid wastes of the by-products of individuals and organizations that are working in vegetable and fruit markets and in various business centers:<br>19.1. Accumulating, placing, and disposing solid wastes outside the compound of the business center or on road sides;<br>19.2. Failure to immediately clean leftover wastes while loading and unloading vegetables and fruits from vehicles;<br>19.3. Failure to collect solid wastes of the business center at its own cost and dispose it at an authorized disposal site or reuse and recycle center by the agency;<br>19.4. Placing wastes of the shop, wrapping materials generated during exchange, chat wastes, cartoons, etc. in front of the shop; | Birr 50,000.00<br>Birr 5,000.00<br>Birr 50,000.00<br>Birr 20,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the area |
| 20 | 20.1. An individual/organization that removes wastes generated from construction or demolishes on an unauthorized place;<br>20.2. A construction owner that harms the surrounding and roads as a result of the movement of cars or loading of soils, mud, demolishes etc. | Birr 5,000.00 for a driver/ **Birr** 50,000.00 for an organization<br>Birr 5,000.00 for a driver/ **Birr** 50000.00 for an organization | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the area |
| 21 | Disposal of bone and meat by-products in an unauthorized place;<br>Individual<br>Organaization | Birr 5,000.00<br>Birr 50,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and remove the waste |

| No. | Types of offenses | Amount of penalty payment | Amount Expected from the perpetrator of the illegal act |
|---|---|---|---|
| 22 | Transporting any dangerous or inappropriate solid waste to a disposal site, incinerator, transfer station, or reuse and recycle center without the permission of the sanitary management agency; | Birr 50,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and take back the waste |
| 23 | Failure to identify used electronic equipment in a special manner and remove it properly in a way that will not harm the environment; | Birr 10,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and remove the waste |
| 24 | Failure to make the area which is found outside of a house or organization green and clean and preserve same:<br>25.1. failure to clear the area outside of the house up to 5 meters radius;<br>25.2. failure to clean the area outside of an organization/institution up to 5 meters radius; | Birr 20000.00<br><br>Birr 100,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the area |
| 25 | An event organizer that organized a timely event and special program who failed to clean the area where the event took place on that same day and immediately after the completion of the program; | Birr 50,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the area |
| 26 | When the concerned owner of a program fails to clean the area, immediately and on the same day, where an annually, monthly, and weekly religious holiday is celebrated; | Birr 20,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the area |
| 27 | Taxi and mini-bus queue controllers, parking service providing organizations, shoe-shiners, weekend street vendors, cattle trading market centers, etc. and organizations/individuals that fail to clean an area of 5 meters radius; | For an individual Birr 2,000.00<br><br>For an organization Birr 20,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the area |

| No. | Types of offenses | Amount of penalty payment | Amount Expected from the perpetrator of the illegal act |
|---|---|---|---|
| 28 | A railway organization that fails to clean solid wastes from the railway lines and train stations | Birr 50,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the area |
| 29 | 29.1. Government offices, non-governmental organizations, religious institutions, schools, business entities, service providing institutions, embassies or an institution/organization that are unable to coordinate its employees and fail to participate in cleaning campaigns which are organized according to the cleaning campaign directive to be issued by the sanitary management agency;<br>29.2. A household that fails to participate in cleaning campaigns which are organized according to the cleaning campaign directive to be issued by the sanitary management agency; | Birr 5,000.00<br>Birr 2,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and participate in the campaign |
| 30 | The failure of any sanitary service providing organization/association/institution to make sure that its employees/members are using safety materials and provide service as per the standards to be issued by the agency or use materials that are below the standard and provide service; | Birr 5,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and use clean safety materials |
| 31 | 31.1. Any sanitary service providing organization that transports and brings unauthorized solid waste by the sanitary management agency to the disposal site, reuse and recycle center or incinerator;<br>31.2. Bringing solid wastes out of the vicinities of the Addis Ababa city administration without the permission of the sanitary management agency; | Birr 50,000.00<br>Birr 100,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and return the solid waste back to its place of departure |

| No. | Types of offenses | Amount of penalty payment | Amount Expected from the perpetrator of the illegal act |
|---|---|---|---|
| | 31.3. An organization/ association/ individual/ institution that fails to cover a solid waste using net or canvas and transport and bring it to disposal sites, reuse and recycle centers or incinerator; | Birr 10,000.00 | |
| 32 | When any private sanitary service providing organization or association collects solid wastes out of its allocated working area or assignment; | Birr 50,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule |
| 33 | When workers carelessly or intentionally water roadside vegetables, soil is thrown onto the road and the road becomes dirty; | Birr 5,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule |
| 34 | If an institution or organization fails to collect waste from the roadside drain pipe for two days | Birr 20,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the area |
| 35 | Any person who paints or writes on a building fence or building fence; posted an advertisement or article; hanging, by an electric or telephone pole; A pillar under a bridge; With earthen retaining walls, For construction fence with fence, Posted notice or text on building fence; | Birr 2000 for individual<br><br>Birr 25000 for organization | Pay the fine indicated in the penalty schedule |
| 36 | Any person who pollutes the area by washing or cause washing a car in an unauthorized straet; | For who washes by themselves Birr 2,000.00<br><br>for who made wash by others 20,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the area |